# የግድግዳው የእጅ ጽሑፍ

ዛሬ ረቡዕ ማታ ስለሆነ፡ ባለፋው ምሽት ቃል ገብቼ ነበር… ጌታ ቢፈቅድ፡ ዛሬ ማታ፡ **የግድግዳው የእጅ ጽሑፍ** በሚለው ርዕስ ላይ እንደምሰብክ፡ ትላንትና ማታ ቃል ገብቼ ነበር። ይህ በጣም፡ ኦህ፡ በዚህ ርዕስ ላይ ለሳምንታት ማውራት እንችላለን፡ ሆኖም ግን ላዩን እንኳን አንዳሰሰውም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ዛሬ ማታ፡ ጥቂት ዋና ዋና ነጥቦችን ለማውጣት እሞክራለሁ። አሁንም ከዳንኤል ምዕራፍ 5 ቁጥር 25፡ ማንበብ እፈልጋለሁ። እንዲህ ይነበባል፥

**የተጻፈውም ጽሕፈት፡ ማኔ፡ ማኔ፡ ቴቄል፡ ፋሬስ ይላል።**

አሁንም ጌታ በንባቡ ላይ በረከቱን ይጨምርበት።

2 እዚህ ያለው ተቆጣጣሪ፡ ጥሩ ወንድማችን፡ እነዚህን ደማቅ መብራቶች ቢያጠፋቸው ብዬ እጠይቃለሁ። እ… መብራቱ በቀጥታ ወደዚህ እየበራ ነው። በጣም፡ አመሰግናለሁ። ጉባኤውን ማየት አልቻልኩም። ማንኛውም ሰው ሳናግር፡ ፊቱን እያየሁ መናገር እወዳለሁ። ከሕዝቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለ ያህል ይሰማኛል።

3 አሁን ጊዜዬን ወስጄ በዚህ ርዕስ ላይ ስለምናገር፡ ዛሬ ማታ፡ በጌታችን እንታመናለን። ይህ ትልቅ ርዕስ እንደሆነ አውቃለሁ። ይህ የወንጌል ሰብከት አገልግሎት ጊዜ-… እንጂ፡ ለመለኮታዊ ፈውስ የተሰጠ አይደለም፡ ሆኖም ለታላቁ መለኮታዊ ፈውስ የተሰጠ ነው። ዛሬ ማታ እኔ የማውቀው፡ በዚህ ምድር ከማንም በላይ በጣም የተመታው አካል፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ነው፥ እጅግ ተቦጫጭቆ፡ ተሰባብሯል፡ ስለዚህ በእውነት መለኮታዊ ፈውስ ያስፈልገዋል።

4 የዛሬ ማታ ርዕሳችን የሚጀምረው በባቢሎን ነው። ባቢሎን በመጀመሪያ የነበረችው፡ አሁንም ያለችው፡ በሰናዖር ምድር ነው። በመጀመሪያ፡ "የእግዚአብሔር ደጅ፡" ወይም **ባቤል** ተብላ ትጠራ ነበር። ባቤል፡ በኋላም **ባቢሎን** ተባለች፡ ትርጉሙም "ግራ መጋባት" ማለት ነው። ባቢሎን በመጀምሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ በዘፍጥረት ውስጥ ትታያለች፡ ከዚያም በመጽሐፍ ቅዱስ መሃል ትታያለች፡ በመጨረሻውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ በራዕይ፡ ውስጥ ትታያለች። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ውስጥ ስላለችም፡ ዛሬም መኖር አለባት።

5 እንዲሁም፡ ዛሬ በምድር ላይ ያሉ፡ መንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ፡ እንደ እግዚአብሔር መንፈስና፡ እንደ የዲያብሎስ መንፈስ የሚባሉ ነገሮች፡ ዛሬ በዓለም ላይ ያሉት ኑፋቄዎችና ነገሮች ሁሉ፡ በዘፍጥረት የጀመሩ ናቸው። **ዘፍጥረት** ማለት "መጀመሪያ" ማለት ነው። እነዚያ ነገሮች ሁሉ፡ ምንም እንኳ በሌላ ስም ወይም በሌላ ቅርጽ ቢሆኑም፡ በዘፍጥረት የጀመረው ያው መንፈስ፡ አሁን እየገለጣቸው ነው። ልክ እንደ ዛፍ እድገት፡ ወደ መጨረሻው እየደረሱ ነው፡ ሁሉም ነገሮች ወደ መደምደሚያቸው የሚደርሱበት፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የሚፈርድበትና የሚቋጭበት፡ ታላቁ የእግዚአብሔር ፍርድ ቀን

ይመጣል። መጀመሪያ ያለው ሁሉ መጨረሻ ይኖረዋል። መጀመሪያ የሌላቸው ነገሮች ብቻ ናቸው መጨረሻ የሌላቸው።

6 ዳግመኛ-የተወለደ ክርስቲያን ፍጻሜ የሌለው ለ—ለዚህ ነው፡ የዘላለም ሕይወት አለውና። ዘላለማዊ ሕይወት የእግዚአብሔር የራሱ የሕይወት ክፍል ነው፡ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነውና። "የእግዚአብሔር ሕይወት" የሚል ትርጉም ያለው፡ በግሪክ ቃል **ዞዊ** ይባላል፡ ኢየሱስ፡ "የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ" ሲል፡ ያው ቃል እንደገና ጥቅም ላይ ውሏል። ስለዚህ፡ አንድ ሰው ዳግመኛ ሲወለድ፡ መንፈሱ ተለውጦ፡ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ፡ የእግዚአብሔር አካል ይሆናል። በእግዚአብሔር መወለዱ፡ በመንፈሳዊ ልደቱ፡ የእግዚአብሔር አካል ስለሆነ፡ እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነ ሁሉ እርሱም ዘላለማዊ ነው።

7 አሁን፡ ባቢሎን የተመሠረተችው የካም ልጅ በሆነው፡ እጅግ ክፉ ሰው፡ በኒምሮድ ነው።

8 ባቢሎን በአንድ ወቅት የዓለም ዋና ከተማ ነበረች። ይህች ታላቅ ከተማ በተገነባች ጊዜ፡ በዙሪያዋ የነበሩት፡ ትናንሽ ከተሞች ሁሉ፡ ለዚህች ታላቅ ከተማ፡ ለባቢሎን፡ ግብርና፡ ቀረጥ፡ ይከፍሉ ነበር።

9 እንደ ሂስሎፕ፡ **ሁለቱ ባቢሎኖች** ያሉ፡ ጥንታዊ መጻሕፍትንና፡ ብዙ ጥንታዊ ታሪኮችን ብታነቡ፡ እዚያ ውስጥ ሁሉም ዓይነት እንግዳ የሆኑ አስተምህሮቶች እንደነበሩ ታገኛላችሁ። በዚያች ከተማ ውስጥ፡ ስሟን አሁን ላስታውሰው የማልችለው አንዲት ሴት ነበረች፡ እርሷም ከምድር እንግዳ... የሆኑ ሥሮችን ታገኝና፡ ከእነርሱ አማልክትን ትሠራ ነበር። ያዕቆብ ከ-እማቱ-የወሰዳቸው አማልክት፡ እነዚያ አንዳንድ የሰር አማልክቶችና፡ የመሳሰሉት፡ እንዲሁም በዓለም ላይ ዛሬ የምናያቸው እነዚህ ኑፋቄዎች ሁሉ እነዚህ ትናንሽ **ኢዝሞች** ከእነዚህ ነገሮች እንደተገኙ ይታመናል። የተፈጥሯቸውንና፡ የዛሬዎቹን ነገሮች ተፈጥሮ ካስተዋላችሁ፡ ተመሳሳይ ነው።

10 ስለዚህ፡ ባቢሎን በዚያ ታላቅና ለም በሆነ ሸለቆ ውስጥ ትገኝ ነበር፡ በኤፍራጥስና በጤግሮስ ወንዞችም ተከባ፡ እንዲሁም መስኖ ታገኝ ነበር። ታላቅ የግብርና ማዕከል ነበረች። ባቢሎንም ታላቅ ከተማ ነበረች። የከተማዋ ዙሪያ፡ በግምት፡ መቶ ሃያ ማይል ያህል ነው፥ በእያንዳንዱ አቅጣጫ ሠላሳ ማይል በመሆኑ፡ ይህም ዙሪያውን መቶ ሃያ ማይል ያደርገዋል። የባቢሎን ከተማ ጎዳናዎች ወደ ሁለት መቶ ጫማ ስፋት እንደነበራቸው ይነገራል። ግንቦቹ ሰማንያ ጫማ ውፍረትና፡ በተግባርም ሁለት መቶ ጫማ ቁመት ነበራቸው። በእነዚህ ግንቦች ዙሪያ፡ በሰረገላዎች የውድድር ሩጫ ማካሄድ ይችሉ ነበር። በሮቹም ከናስ የተሠሩ ነበሩ፡ እነዚያም በሮች ሁለት መቶ ጫማ ስፋት ነበራቸው። በከተማዋ መሃል ቤተ መንግሥቱ ይገኝ ነበር፡ ቤተ መንግሥቱም የዙፋኑ ስፍራ ነበረ። በከተማዋ መሃልም፡ ታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ ይፈስ ነበር። ብታስተውሉት፡ ይህች የዲያብሎስ ከተማ ናት፡ ምክንያቱም በዙፋኑ ፊት እንዳለው የሕይወት ወንዝ፡ በእግዚአብሔር ከተማ አምሳል የተቀረጸች ናትና። በከተማዋ ውስጥ፡ በግንቦቹ ዙሪያ፡ ታላላቅ፡ የተንጣለለ፡ የአትክልት ስፍራዎች ነበሯቸው።

11 በወቅቱ የሚታወቀውን ዓለም ሁሉ አጥፍቶ፡ ሁሉም ዓለም፡ ግብር ይገብርለት የነበረ፡ ታላቅና ኃያል መንግሥት ነበር። በሳይንስም እጅግ የገፉ ሲሆን፡ ሳይንስ ሊያመርታቸው የሚችላቸውን ዘመናዊ ነገሮች ሁሉ ነበሩት። ዘመናዊ ሰረገላዎች፡ ሞደርን ዲዛይኖች፡ ከባድ የጦር መሳሪያዎችና፡ ምርጥ ብረታ ብረቶች ነበሩት። ለተቀረው ዓለም እጅግ አስደናቂ ነበር።

12 ዛሬ ምሽት በምንነጋገርበት፡ በዚህ ክስተት ወቅት ንጉሥ ብልጣሶር በእነዚህ ግንቦች ውስጥ ንጉሥ ነበረ። ንጉሥ ብልጣሶር፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፡ “አባቱ፡ ናቡከደነፆር ነበር፡” እውነቱ ግን እርሱ የተካው አያቱን፡ ንጉሥ ናቡከደነፆርን ነበር።

13 ናቡከደነፆር የአሕዛብ መንግሥታት መጀመሪያ፡ የወርቁ ራስ እንደነበረ ብዙዎቻችሁ ታስታውሳላችሁ። እርሱም ብዙ፡ ብዙ ማይሎች ርቃ ወደምትገኘው፡ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ፡ አይሁዳውያንን ማርኮ ወደ መንግሥቱ አምጥቷቸው ነበር፡ ባሪያዎችም አደረጋቸው፡ ሊቃውንቶቻቸውንም ተጠቀመባቸው ወዘተረፈ።

14 ልክ ሩሲያ ወደ ጀርመን በገባች ጊዜ እንዳደረገችው ነው። አቶሚክ ቦምብንና፡ የመሳሰሉትን ያገኙት፡ እነዚያን የጀርመን ሳይንቲስቶች ስለማረኩ ነው። ዛሬም እንዲህ በጣም የረቀቁት፡ እነርሱን ማርከው ወደዚያ ስለወሰዷቸው ነው። ራሳቸው፡ አልነበራቸውም፡ ነገር ግን ልክ ናቡከደነፆር በአይሁዳውያን ላይ እንዳደረገው ሄደው እነዚያን ነገሮች አገኟቸው።

15 በዚህ ጊዜ፡ ዳንኤል የተባለ፡ የጌታ ነቢይ የሆነ ጻድቅ ሰው፡ በምርኮ ተወስዶ እንደነበር፡ ደርሰንበታል። እርሱም በንጉሥ ናቡከደነፆር ዘመነ መንግሥት በኮከብ ቆጣሪዎችና፡ በመሳሰሉት፡ በጠቢባንና በሰብአ ሰገል ሁሉ ላይ፡ እደ አለቃ ሆኖ አገልግሏል።

16 አሁን ደግሞ ብልጣሶር ሥልጣኑን ተረከበ። ብልጣሶር ክፉ ዓይነት ሰው ነበረ። ግድ የለሽ ነበረ።

17 የባቢሎን ሰዎችም ያላቸው የሚመስላቸው፡ እንዲህ ዓይነት ደኅንነት ነበራቸው! እንዴ በእነዚያ በሮች ከገቡና፡ በሮቹ ከተዘጉ በኋላ፡ በዚያ ሁለት-መቶ-ጫማ ቁመትና፡ ሰማንያ ጫማ ውፍረት ባለው፡ ግንብ ውስጥ ምን ያህል ደኅንነት እንደተሰማቸው እስቲ አስቡት!

18 ነገር ግን ይህንን አስታውሱ፥ ሳይንስ ምንም ያህል ደኅንነት ቢሰጣችሁ፡ ኃጢአት ስትሠሩ እግዚአብሔር ያገኛችኋል! ብቸኛው መሸሸጊያ አንድ አለ፡ እርሱም በክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

19 አሁን፡ ልክ እኛ እንደምንኖርባት እንደዚች ድንቅ አሜሪካ፡ እነርሱም የዓለም መሪ አገር በመሆናቸው፡ ዘመናዊ ሥልጣኔያቸው ታላቅነት እንዲሰማቸው አድርጓቸው ነበር። እኔም ራሴ ያሳሰበኛል፡ እነርሱ የነበራቸውን ዓይነት አመለካከት እኛም እየያዝን እንዳይሆን፡ እሰጋለሁ። እኛም ምርጥ፡ ሳይንቲስቶች፡ ምርጥ መትረየሶች፡ አቶሚክ ቦምቦችና፡ በጣም ፈጣን አውሮፕላኖች አሉን፡ ብለን ስለምናስብ፡ እንዲሁም... የዓለም መሪ አገር በመሆናችን፡ በሆነ መንገድ ያለ እግዚአብሔር ደኅንነት እንዳለን ተሰምቶናል።

20 ይህ በጣም ግልጽ የሆነ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ፈጽሞ አይለወጥም። ለኃጢአት ያለው አመለካከት ያን ጊዜ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ያው ነው። እዚህ ምድር ላይ ምንም ዓይነት መደበቂያ የለም። ደኅንነታችሁ በክርስቶስ ብቻ ነው።

21 በዚች ታላቅ ከተማ ውስጥ፥ የትኛውም ሠራዊት ከተማይቱን ሊወራት የሚችልበት፥ ምንም ዓይነት መንገድ፥ በዓለም ላይ ያለ አይመስላቸውም ነበር። እነዚያ ታላላቅና፥ ረጅም ግንቦች፥ ዘመናዊ ትጥቆቻቸው፥ ከውጭው ዓለም ተለይተው እንዲቀመጡ አድርጓቸዋል። ነገር ግን ሜዶንና ፋርስ የተባሉ ክፉ ሕዝቦች፥ አሁን የሕንድ ሂንዱዎች የሚባሉት፥ ከከተማው ግንብ ስር ሾልከው ለመግባት እንዲችሉ፥ የኤፍራጥስን ወንዝ አቅጣጫ ለመቀየር፥ ማይሎች ርቀው የወንዝ ቦይ እየቆፈሩ እንደነበረ አያውቁም ነበር። ደኅንነት ይሰማቸው በነበረበት በዚያ ሰዓት! ሁልጊዜም የሚሰማቸው ያ ነበር። ደኅንነት በተሰማቸውም ቁጥር፥ በኃጢአት ውስጥ ይዘፈቁ ነበር።

22 አንድ ሰው ራሱን-እንደቻለ በሚሰማበት ደረጃ ላይ ሲደርስ፥ ኃጢአት ሊቆጣጠረው የሚጀምር ይመስላል። የትኛውም ቤተ ክርስቲያን፥ አገር፥ ወይም ግለሰብ፥ ከውጭ የሚመጣ እርዳታ እንደማያስፈልገው በሚሰማው ጊዜ፥ ኃጢአት በእርሱ ውስጥ መንገሥ ይጀምራል። እውነት ነው። ካስተዋልን፥ ሰዎች የልህቀት ስሜት ሲሰማቸውም፥ ጭምር፥ ብዙውን ጊዜ ኃጢአት ገብቶ ይበላቸዋል።

23 ስለዚህ እነዚያን በሮች ሲዘጉ፥ ደኅንነታቸው የተጠበቀ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ከሰማያት ሆኖ ተመለከተ! “ኃጢአትም ለማንኛውም ሕዝብ ነቀፋ ነው።”

24 ዛሬ ማታ፥ እገረማለሁ፥ ባለን ታላቅ መሣሪያ ሁሉ፥ በአቶሚክ-ኃይል በሚሰሩ ሰርጓጅ መርከቦቻችን፥ እንዲሁም በሰከንድ፥ ወይም፥ በደቂቃ ብዙ መቶ ማይሎችን በሚበሩና፥ የድምፅን ፍጥነት እንኳን ማለፍ በሚችሉ፥ ጄት አውሮፕላኖቻችን ተማምነናል። ነገር ግን፥ ኃጢአታችሁ እንደሚያገኛችሁ ከቶ አትዘንጉ!

25 በዚህ ጊዜም፥ በሮቹን፥ ዘግተው ነበር። የተጠበቁ ስለነበሩም፥ እንደፈለጉት በፈንጠዚያ በድግስ መኖር የሚችሉ፥ መስሏቸው ነበር። መሪ አገር ስለነበሩ፥ ሌሎች አገሮች ሁሉ ለሳይንስና ለ—ለእርዳታ እነርሱን ይመለከቱ ነበር።

26 እናም፥ በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ፥ ይህ ንጉሥ ትልቅ አሰደሳች ጊዜ የሚያሳልፍ መሰሎት ነበር። ለታላቅ ጭፈራ፥ ወይም፥ እኔ እንደምለው፥ ለዘመናዊው ሮክ-ኤንድ-ሮል ቀጠሮ ያዘ፥ ከዚህ የተለየ አልነበረም። ስለዚህ ሰዓቱን ወሰነ፥ ታዋቂ ሰዎችን ሁሉ፥ ወታደሮችንና አዛዦችን፥ ሚስቶችንና ቁባቶችንም ሁሉ ጋበዘ።

27 አሁን፥ ቁባት ማለት ሕጋዊ አመንዝራ ማለት ነው። አንድ ሰው ለራሱ-በቂ እንደሆነ ማሰብ ሲጀምር፥ እንዴት በኃጢአት መዘፈቅ እንደሚጀምር፥ አያችሁ?

28 ሊያገኝ የሚችለውን ምርጥ መጠጦች ሁሉ፥ ለሚያዘጋጀው ለዚህ ትልቅ የሮክ-ኤንድ-ሮል ድግስ የሚሆን አሰመጣ። ደኅንነቱ የተጠበቀ መሰለው። የተጠበቀ ስለነበረም፥ የሚጎዳው ምንም ነገር ያለ አልመሰለውም። ይህንንም ታላቅ ድግስ ከቤተ መንግሥቱ ጀርባ ባሉት አትክልት ስፍራዎች ውስጥ

አደረገ። በዚያም በአትክልት ስፍራው ውስጥ፡ ምናልባት ሁሉንም ነገር በሚያምር ሁኔታ አሸብርቀውት፡ ጌጣጌጦችን ሁሉ ሰቅለው፡ ወታደሮቹን የሚያዝናኑ የተውኔት ልጃገረዶችና ብዙ ሴቶችን፡ ከቢራና ከወይን ጠጃቸው ጋር አምጥተው ነበር። ይህ ዛሬ ላለው የሮክ-ኤንድ-ሮል ፓርቲ ጥሩ ዘመናዊ ምሳሌ ካልሆነ፡ ሌላ የት ሊገኝ እንደሚችል አላውቅም። በትክክል እንደዛው ነው። ሁሉንም ነገር አዘጋጁ፡ ታላቅ ድግሰም ሊያደርጉ ነበር።

29 ብዙ ያገቡ ሴቶች እንደመጡ ምንም ጥርጥር የለውም። እነርሱ ለመዝናናት ሲወጡ፡ ባሎቻቸው ልጆችን እየጠበቁ ቤት ቀርተዋል። በተቃራኒው ደግሞ፡ የሰከረ ባል ለመዝናናት ሲወጣ፡ አንዲት እናት የታመመ ሕፃን ይዛ፡ ቤት ሳሎን ስትመላለስ ስትጨነቅ እንደነበረች ጥርጥር የለውም። ሁለቱም አንድ ናቸው፡ ይህኛው የዚያኛው ነፀብራቅ ነው።

30 መጠጣትና መደሰት ሲጀምሩ ይታዩኛል። ባንዱም ድምፁን ከፍ አድርጎ፡ ሙዚቃውን መጫወት እንደጀመረ እገምታለሁ። አፍላ ወጣቶችም እርስ በርስ እየተወዛወዙ ይጨፍራሉ። የሰከሩትም፡ ወታደሮች፡ ሴቶቹን እየያዙ ወደላይ እየወረወሩ ይሰሟቸዋል፡ ወንበራቸው ላይም እየተቀመጡ፡ ይጮኻሉ፡ ደኅንነታቸው የተጠበቀ መሰሏቸው ነበር።

31 አንቺ፡ አሜሪካ ሆይ፡ የሰከረው የሮክ-ኤንድ-ሮል ፓርቲሽን የተመለከተው፡ ይህ እግዚአብሔር፡ ዛሬ ማታ አንቺንም እየተመለከተሽ ነው!

32 ምን ዓይነት አስደሳች ጊዜ እያሳለፉ እንደነበር መገመት ትችላላችሁ! ይህ ብልጣሶር የተባለ ንጉሥ፡ የዘመናችን ኤልቪስ ፕሬስሊ እንደነበረ፡ እገምታለሁ፡ እነርሱ ያደርጉት የነበረውን ብዙ ድንቅ ነገሮች ሊያደርግ ይችል ነበር። ያ ሁሉ ነገር ሲቀጥል፡ በዚያ ሁሉ ጊዜ፡ ሞት በደጃቸው እንደነበረ፡ በጭራሽ አያውቁም ነበር!

33 ስለዚህ፡ ልክ እንደ ዘመናዊው የሆሊውድ የቴሌቪዥን ሰርጭት ድባብ ሁሉ፡ ድግሱ በደንብ ሲሞቅ፡ በሃይማኖታዊ ጉዳይ አንዳንድ ቀልዶችን ለመቀለድ አሰቡ፥ ልክ እንደ አርተር ጎድፍሬይ አለባበስ፡ ወይም ዛሬ እንዳሉ ዘመናዊ ነገሮች፡ ወይም እንደ ኤርኒ ፎርድ ፒ-ፒከር፡ ስለ ሰባኪው የሆነ ቀልድ ቀለዱ። ነገር ግን እግዚአብሔር አሁንም ከሰማይ ሆኖ ወደ ታች ይመለከታል! እነርሱ ግን በማይነካ አገር ውስጥ ያሉ መሰላቸው። ነገር ግን የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ!

34 ሰዎች ሆይ፡ ይህንን ብቻ እወቁ። አገር ብትሆኑ፡ ወይም ቤተ ክርስቲያን፡ ወይም ግለሰብ፡ የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ!

35 ይህም፡ ንጉሥ ቆሞ፡ እንዲህ ሲል ይታየኛል፡ "እስቲ አንዴ ጸጥ በሉ፡ ሴቶች፡ እስኪ በሰባኪው ላይ አንድ ጥሩ ቀልድ እንቀልድበት፡" ወይም ወዘተ።

36 ወጣት ሴቶችም፡ ጌጣጌጣቸውን እየ፡ "እሰይ! አዎ፡ ያንን መሰማት እንፈልጋለን" ይላሉ።

37 ወጣት ወታደሮቹም ልክ እንደ ዛሬው ዘመን ጎረምሶች ሆኑ፡ ምክንያቱም ይህ ከዘመናዊ ባቢሎን የተለየ አይደለምና! እኔ አሜሪካዊ ነኝ፡ ዳንኤልም ግን በዚያን ጊዜ የባቢሎን ዜጋ ነበረ። ያ ግን ለኃጢአት ምክንያት አይሆንም!

አንድ ጊዜ አንዲትን ሴት፡ "ክርስቲያን ነሽ" ብዬ ጠየቅኳት?

እሷም፡ “እንድታውቅልኝ የምፈልገው፡ እኔ አሜሪካዊ ነኝ” አለችኝ።

እኔም፡ “ያ’ማ ምንም ማለት አይደለም” አልኳት። በጭራሽ!

38 አሜሪካዊ በመሆኔ ደስ ይለኛል፡ ነገር ግን ያ ከክርስትናን ከማንጸባረቅ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም፡ ምንም። ኃጢአት ከሠራን፡ ለኃጢአታችን ዋጋ እንከፍላለን፡ ይህንን በእርግጠኝነት እወቁት።

39 በዚያም ነቢይ ነበራቸው፡ ሆኖም ሊሰሙት አልፈለጉም። መልእክቱም ነበራቸው፡ ዳሩ ግን በእርሱ ላይ ማላገጥ ፈለጉ።

40 ይህ የዛሬዋን አሜሪካ ካልሆነ፡ ሌላ ምን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም። ወንጌሉና፡ እውነቱ አላቸው፡ ነገር ግን በእርሱ ማላገጥ ይወዳሉ።

41 ስለዚህ እንዲህ አሉ፡ “ሂዱና የነዚያን ሆሊ-ሮለሮች ዕቃዎች አምጡና፡ እዚህ በእነርሱ ላይ እናላግጥ” አሉ።

42 እግዚአብሔር ኃጢአተኞች በሕዝቡ ላይ እንዲቀልዱ አይፈቅድም! አንድ ቀን፡ ለዚህ ዋጋ ትከፍላላችሁ።

43 የጌታንም ዕቃዎች ሄደው አመጡና፡ ወደ ቤተ መቅደሱ አገቧቸው፡ በጌታም ዕቃዎች ጥሩ መጠጥ ሊጠጡ ነበር። ኦርቴልስ 92 ወይም ፓብስ ብሉ ሪቦን፡ በውስጡ ቀድተው፡ እየቀዱበት ለመቀለድ፡ ኦህ፡ ጽዋዎቹንና ዕቃዎቹን እያጋጩ፡ መጠጣት ጀመሩ፡ በጌታም ሃይማኖት ላይ እየሳቁ አላገጡ። ምን እያደረጉ እንደሆነ አያውቁም ነበር።

44 ዛሬ ምሽት፡ ይህችም አገር፡ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን መልእክትን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዳግመኛ መወለድን ውድቅ በማድረግ፡ ባለማወቅ ውስጥ ናት።

45 ምንም እንኳ ሃይማኖተኞች ቢሆኑም፡ አሁን፡ ያ የሰከረ የሮክ-ኤንድ-ሮል ድግስ፡ ሃይማኖተኞች ነበሩ፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ፡ “አማልክቶቻቸውን ያመሰግኑ ነበር” ይላልና።

46 ስለዚህ እጅግ በጣም ሃይማኖተኛ ሆናችሁም እንኳ፡ ልትሳሳቱ ትችላላችሁ! በትክክል። ቅንነት ብቻውን በቂ አይደለም። “ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፡ ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ናት።” ስለዚህ፡ እነርሱ የሚያመልኩበት፡ ታላቅ የመንግሥት ቤተ ክርስቲያንና ሃይማኖት ነበራቸው፡ ሆኖም በእግዚአብሔር ቅዱስ ነገሮች ላይ አላገጡ።

47 ይህም ዛሬ በእግዚአብሔር ቅዱስ ነገሮች ላይ የማላገጥ፡ ትክክለኛ ምሳሌ ነው። ንጹሕና ጨዋ፡ ቅን ሆነው ለመኖር፡ የሚሞክሩትን ሰዎች፡ “ያለፈበት ፋሽን” ወይም “ሆሊ ሮለር፡” ወይም ደግሞ በሌላ አሳፋሪ ስም ይጠሯቸዋል። ጌታ የሚያደርጋቸውን፡ የጌታ ስጦታዎች ደግሞ እንደ እንደ ሰይጣን ሥራ፡ በርኩስ መንፈስ እንደሚደረግ አድርገው ይቆጥሩታል። ኦህ፡ ታዲያ ከፍርዱ እንዴት ታመልጣላችሁ? የሰማዕታት ደም ለዚህ ይጮኻልና! እግዚአብሔር ይህችን አገር ስለ ዘመናዊ ኃጢአቷ ካልፈረደባት፡ ሰዶምና ገሞራን ቀሰቅሶ፡ ስላጠፋቸው ይቅርታ መጠየቅ ይኖርበታል። በትክክል። ወደ ፍርድ እያመራን ነው! የምታዩዋቸው እነዚህ የተባረከው አዳኛችን የሚያደርጋቸው ታላላቅ ድንቆች፡ ፍርድ በደጃፍ መሆኑን የሚያሳዩ፡ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ናቸው፥ እርሱም ይህችን አገር ከዳር እስከ ዳር፡ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፡ ከሰሜን

እስከ ደቡብ አዳርሷታል። እነርሱ ግን ይንቁታል፡ ይስቁበታል፡ ይተቹታል፡ በጋዜጦቻቸውም እንደ “ከንቱ” ነገር ይጽፉታል። እስቲ አስቡት፡ ዘመናዊቷ ባቢሎን!

48 አሁን እየጠጡና፡ ጽዋዎቻቸውን እያጋጩ ሳሉ፡ በድንገት፡ ይህ ብልጣሶር የተባለው፡ ታላቅ የፊልም ተዋናይ፡ ከጽዋው ሊጠጣ ሲል፡ ዓይኖቹ ሊወጡ ደረሱ፡ ዘወር ብሎም ወደ ግንቡ ሲመለከት፡ ከሰማይ፡ የወረደ፡ የሰው እጅ አየ፡ እርሱም በግድግዳው ላይ ወደ ላይና ወደ ታች መጻፍ ጀመረ።

49 ልብ እንድትሉ የምፈልገው፡ በተለሰነው ግድግዳ ላይ እንደጻፈ ነው። አሁን፡ ምናልባት የሮክ-ኤንድ-ሮል ጭፈራቸውን በሚያካሂዱበት ሰፍራ፡ ጌጣጌጦቹ መሃል መቅረዞች ተቀምጠው፡ ብርሃናቸው ግድግዳው ላይ ያርፍ ነበር። እግዚአብሔር ነገሮችን ጥግ ይዞ አያደርግም!

እግዚአብሔር የሚናገረውና የሚንቀሳቀሰው በብርሃን መካከል፡ ግልጽ በሆነ ቦታ ነው። ስለዚህ የእርሱ መለኮታዊ ጽሕፈት በሁሉም ፊት ግልጽ ሆኖ፡ በተለሰነው ግድግዳው ላይ ታየ።

50 አስቀድሞ ያየው፡ ይህ ዘመናዊ ፊዘኛ፡ የሬዲዮ ኮሜዲያንና፡ የቴሌቪዥን ተዋናይ የሆነው ንጉሥ ሳይሆን አይቀርም። ሊጠጣ፡ ብርጭቆውን፡ ወይም በእጁ የያዘውን ጽዋ፡ ከፍ ሲያደርግ፡ ዓይኖቹ ፈጠጡ፡ ሰውነቱም ሁሉ ተናወጠ። ምን እንዳደረገ መገመት እችላለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “አጥንቶቹም ከመገጣጠሚያው፡ ላሉ” ይላል። በእርግጥም፡ ክፉኛ ተናውጦ ነበር። እግዚአብሔር ምልክቶቹን ማሳየት ሲጀምር፡ መናወጥ የሚጀመርበት ጊዜ ነው። በትክክል። እንዳስተዋለውም፡ ያ የሮክ-ኤንድ-ሮል ዘፈኑ እንዲናወጥ አደረገው።

51 በግድግዳው ላይ ያለውን ይህን ጽሕፈት ሲመለከት፡ ያቺ ምስኪን ሚስቱን ከንፈሯን ቀለም ተቀብታ ምን አይነት እንደሆነ አላውቅም፡ ጸጉሯ በጌጣጌጥ አሸብርቆና፡ እየተወዛወዘች፡ ከሰከሩት ወታደሮች ጋር ሆና፡ ሰቅ እያላት፡ “ዛሬ ምሽት ልጁን ምን ነካው? ” ስትል ማሰብ እችላለሁ።

52 አንድ ወጣትም ያዛትና፡ “እሺ፡ የሚቀጥለውን አብረን እንጨፍር፡” ይላታል። ሙዚቃውም ቆመ።

53 ኦህ፡ አንቺ ታላቅ ኃጢአተኛ ሀገር፡ አንድ ቀን የሮክ-ኤንድ-ሮል ጭፈራሽ መቆሙ አይቀርም! የሰባኪውን ድምጽ ካልሰማሽ፡ አንድ ቀን በፍርድ የእግዚአብሔርን እጅ ትሰሚያለሽ። ነገር ግን የሮክ-አንድ-ሮል ጭፈራው ይቆማል፡ ያ የሙዚቃ ባንድ እንደተጫወቱት፡ ልክ በታይታኒክ መርከብ ላይ **አምላኬ ሆይ፡ ወደ አንተ፡ እቀርባለሁ** ብለው እንደተጫወቱት ያቆማል። አንድ ቀን ያንን ዜማ ትቀይሪያለሽ።

54 ሙዚቃውም ቆመ፡ እነርሱም ያንን ቀልደኛቸውን፡ በ—በቴሌቪዥን ስክሪናቸው ላይ የሚያዩትን፡ ኮከባቸውን ተመለከቱ፡ እርሱም ይህ ታላቅ ነገር ሲከናወን እያየ፡ ጉልበቶቹ እርስ በርስ እየተላተሙ ቆሞ ነበር፡ እርሱም እንዲህ አለ፡ “ለምን፡” “ግንቦች ሁሉ በዙሪያው ተዘግተዋል! ምርጥ የሆኑት ጠባቂዎቼ፡ በበሩ ላይ ቆመዋል እኮ።”

55 ነገር ግን፡ እያችሁ፡ እግዚአብሔር እናንተ እንደምታስቡት በበሩ መግባት አያስፈልገውም። ከክብር ከላይ ይወርዳል! እጁም በግድግዳው ላይ ይጽፍ ነበር።

56 በዘመናዊ ሰፍራ እንደመሆኑ፡ ፈጥኖ፡ መተንበይ የሚችሉትን፡ ኮከብ ቆጣሪዎችን፡ ቢሾፖችን፡ ጳጳሳትን፡ ዶክተሮችን፡ ካርዲናሎችንና፡ የመሳሰሉትን ሁሉ ጠራ። እንዲህም አላቸው፡ “አሁን እናንተ የከበራችሁ ሰዎች፡ እነግራችኋለሁ፡ እንደፈለጋችሁ እንድታደርጉና እንድትሰብኩ እድል ሰጥቻችኋለሁ። አሁን ግን፡ ግድግዳው ላይ ያለውን፡ ተርጉሙልኝ።”

57 ልክ ያኔ እንደነበረው ሁሉ፡ ዛሬም እንደዚያው ነው፡ ከተፈጥሮ በላይ ከሆነ ነገር ጋር ልምምድ አልነበራቸውም። ስለ እርሱ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ልሳኖችን እንዴት መተርጎም እንደሚቻል አያውቁም ነበር። ስለ ሰማያዊ ቋንቋ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ፈጽሞም ግራ ተጋቡ። ምንም አያውቁም ነበር። እዚያም ቆመው ሳለ...

58 አስታውሱ፡ ይህ የአሕዛብ መንግሥት አጀማመር ነው። ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ እንደጀመረ፡ ፍጻሜውም በዚያው በተአምራዊ መንገድ ይሆናል።

59 ነገር ግን እነዚህ ጳጳሳትና ካርዲናሎች፡ ታላላቅ ዶክተሮች፡ መለኮታዊውን ነገር መተርጎም አልቻሉም። ስለ እርሱ ምንም አያውቁም ነበር። ሁሉንም የጥበብ መጽሐፎቻቸውን ቢመለከቱም፡ ከእርሱ ጋር የሚወዳደር ምንም ነገር አላገኙም። እያችሁ፡ መንፈሳዊ ነገር በመንፈሳዊ መንገድ ነው የሚረዳው። ከዚያም ሁሉም ተረበሹ፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸውም አላወቁም ነበር።

60 በመጨረሻም፡ አንዲት ንግሥት፡ አስታውሱ፡ እርሷ በሮክ-አንድ-ሮል ጭፈራው ላይ አልነበረችም፡ የሆነ ነገር እየተካሄደ መሆኑን ያወቀችበት ብቸኛው መንገድ፡ ንጉሡ በጣም እንደተረበሸና ጭፈራው እንደቆመ ዜና ወደ እርሷ ስለደረሰ ነበር። እርሷ ከጥሩ እማኞች አንዷ ልትሆን ትችል ነበር። እናም፡ **በሆነ መንገድም**፡ ያለፈውን ያልረሳች ነበረች።

61 ወደ ድግሱ በፍጥነት ገባች። ያ ዘመናዊ ቀልደኛና ቡድኑ ሁሉ፡ በጣም ተረብሸው ባየች ጊዜ፡ “ንጉሥ ሆይ፡ ለዘላለም ንገሥ፡” አለች! ሆኖም ያኔውኑ የሞተ መሆኑን አላወቀም ነበር። እንዲህም አለች፡ “ለዘላለም ንገሥ! በግድግዳው ላይ ባለው በዚያ የእጅ ጽሑፍ ሁላችሁም እንደተጨነቃችሁ አውቃለሁ። ጳጳሱን፡ ኤጲስ ቆጶሳቱንና ካርዲናሎቹን፡ እንዲሁም የሥነ መለኮት ዶክተሮቹን አይቻለሁ፡ ከእነርሱም አንዱ እንኳ ሊያነበው አልቻለም። ዳሩ ግን ኦ፡ ንጉሥ ሆይ፡ አንድ ነገር ልንገርህ! በመንግሥትህ ውስጥ ከተፈጥሮ በላይ ስለሆነው ነገር የሚያውቅ፡ አንድ ሰው አለ።”

62 ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ዛሬ፡ በግድግዳው ላይ ያለውን የእጅ ጽሑፍ ሰናይ፡ ስለ እርሱ የሚያውቅ አንድ ሰው ግን አለ። በከተማው ውስጥ ባሉ የዶክተሮች ቢሮዎች ሁሉ አልፈህ ሊሆን ይችላል፡ እነርሱም፥ “መሞትህ አይቀርም” ብለውህ ይሆናል። ዳሩ ግን አንድ ሰው አለ! ነፍሳችሁ እንደ ሲኦል ጥቁር ግድግዳዎች እስክትጠቁር ድረስ በኃጢአት ውስጥ ተነክራችሁ፡ ያለ ምንም ተስፋ፡ ራሳችሁን ለማጥፋት ተዘጋጅታችሁ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንድ ሰው አለ፡ ስሙም ኢየሱስ ነው! እርሱ ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን ያውቃል። እኛ

የመንግሥቱ ልጆች ስለሆንን፡ እርሱ በእኛ መንግሥት ውስጥ አለ። አንድ ሰው አለ!

63 እንዲህም አለች፡ "እርሱ ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን ያውቃል፡ ከዓመታት በፊት የእግዚአብሔርን መንፈስ በእርሱ ውስጥ አግኝተውበታልና። የተዋጣለት መንፈስም ነበረው። ሕልሞችን መተርጎም ይችላል፡ ራእዮችን ያያል፡ እያንዳንዳቸውም ትክክል ነበሩ። ስለዚህ፡ አትጨነቅ፡ ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ ስጠኝና እዚህ አመጣዋለሁ።"

64 እርሱን የምትጠሩበት አንድ ቀን ይመጣል! በቤታችሁ ውስጥ ለእርሱ ምንም ቦታ ላይኖራችሁ ይችላል። ቴሌቪዥን በማየት፡ ካርታ በመጫወት፡ ቢራ በመጠጣት፡ በሮክ-አንድ-ሮል ድግሶች በመገኘት፡ ተጠምዳችኋል። ነገር ግን እርሱን የምትጠሩበት አንድ ጊዜ አለ! ይህ እውነት ነው።

65 ስለዚህ ዳንኤል ወደ ውስጥ ገባ። ወደ ውስጥ ሲገባም... የጽድቅ ሰባኪ፡ የእግዚአብሔር ሰው ነበረ! ያንን ነገር ሳይቃወም የእግዚአብሔር ሰው እንደዚያ ባለ ቦታ ውስጥ ይኖራል ብዬ ማሰብ አልችልም። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ንጉሡ ለዚያ ምንም ትኩረት አልሰጠም ነበር፡ ለዚህም ነው አሁን ባለበት ሁኔታ ላይ የሆነው።

66 ዳንኤልንም አመጡት፡ እርሱም እንዲህ አለ፡ "ሊቀ ጳጳሳቶቻችሁና ሊቃውንቶቻችሁ ለምን ሊተረጉሙላችሁ አልቻሉም?" እነርሱ የሚተረጉሙበት ምንም ነገር አልነበራቸውም።

67 ታዲያ ምን ተፈጠረ? ዳንኤል እንዲህ አለ፡ "ኦህ፡ ብልጣሶር ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ታውቅ ነበር። ከአንተ አልተሰወሩም።"

68 እኔም ለአሜሪካ እላለሁ! በዚህች ቅጽበት፡ ድምፄን እንዲሰሙ ማድረግ ብችል፡ ደስ ባለኝ ነበር። እናንተም እነዚህን ነገሮች ሁሉ የማታውቁ አይደላችሁም! ከእኛ በፊት የነበሩ አገሮች ኃጢአት እንደሠሩና እኛም ያንኑ እንዳደረግን ሁሉ፡ በሚዛን ተመዝነን፡ ቀልለን ተገኝተናል። ፈረንሳይ ምን ሆነች? ጀርመን ምን ሆነች? "በወይን ጠጅ፡ በሴቶችና፡ ታላቅ ጊዜ በማሳለፍ" የተዘፈቁት ሌሎች አገሮችስ ምን ሆኑ? ነገሩ ሁልጊዜም በዚህ መንገድ ነው የሚያበቃው፡ እኛም ከፍርድ ነጻ አይደለንም። እግዚአብሔር ጻድቅ ነውና።

69 እንዲህም አለው፡ "አባትህ፡ እግዚአብሔር እንዴት ታላቅ ሕዝብ እንዳደረገው፡ እርሱ ግን ዘነጋው። አንተም አሁን እንደምታደርገው ያንኑ ሰላደረገ፡ እግዚአብሔር ወደ አራዊትነት ለወጠው።" እንዲህ አለ፡ "እነዚህን ነገሮች እያወቅህ፡ ነገር ግን የእርሱን ቅዱሳን ዕቃዎች ወስደህ አላገጥክባቸው" አለ። አስተውሉ፡ እንዲህ አለው፡ "ጽሕፈቱ በግድግዳው ላይ ሰፍሯል፡ አሁን መንግሥትህ ተቆጥሯል።" በሌላ አነጋገር፡ "ተመልከት፡ ወዳጄ፡ ቀኖችህ ተቆጥረዋል! መንግሥትህ ተወስዶ ለሌላ ሕዝብ፡ ጨካኝና፡ እግዚአብሔርን ለሌለበት ሕዝብ ተሰጥቷል፡" ይህም ልክ እንደ እነርሱ ክፉ የሆነ ሕዝብ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአትን በኃጢአት እንዲዋጋ ያደርገዋል። ዛሬም፡ እንዲህ...

70 በትክክል በዚያው ቅጽበት፡ በመጀመሪያ አንድ ነገር ልናገር፡ ግድግዳው ላይ ያለውን ያንን ጽሑፍ እያየ፡ በዚያ በቆመ ጊዜ፡ ልክ በዚያው ሰዓት፡ በሮች ስር የነበሩት ጠባቂዎች እንደተገደሉ፡ ጨርሶ አያውቅም ነበር። ወታደሮቹ በጎዳናዎች ላይ ነበሩ፡ የቤተ መንግሥቱንም ጠባቂዎች እየገደሉ ነበር።

በደረጃዎቹ ላይ ደርሰው ነበር። እነዚያም ሴቶች እዚያ ቆመው፡ ከልጆቻቸውና፡ ከባሎቻቸው ተለይተው፡ ባሎች ከምስቶቻቸው ተለይተው፡ ሰክረው፡ የሆነ ዓይነት ዘመናዊ ጭፈራ እያዳመጡ ነበር። ወታደሮቹም ደረጃዎቹ ላይ ነበሩ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥም ንጉሡ ይገደላል። ያ ሁሉ ሰካራም የሰው ሰብሰብ፡ በአንድ አምላክ የለሽና፡ በዲያብሎስ-በተያዘ ሕዝብ ይገደላል። ሴቶቹም ወጣት ልጃገረዶችም ጭምር፡ ልብሳቸው ተገፍፎ፡ በጎዳናዎች ላይ ይደፈራሉ፡ ከዚያም እግራቸውን ይዘው በግድግዳ ላይ እየደበደቡ፡ ጭንቅላታቸውን ይፈነካከቷቸዋል፡ በፍትወት ከእነርሱ ጋር አብረው ከኖሩ በኋላም በሰይፍ ይገነጥሏቸዋል። እብድና፡ የሰከሩ ወታደሮች! በሚዛን ተመዝነው፡ ቀልለው ተገኝተዋልና፡ በደጃፍ ላይ ነበረ።

71 ዛሬም፡ በዚህ ሁሉ ዘመናዊ-እንቅስቃሴያችን፡ በፈውስ አገልግሎቶች ላይ፡ በመሳለቅና በማላገጥ፡ በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ላይ በመሳቅና በማላገጥ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚሆኑ እንደተናገረውን በማድረግ፡ “ትዕቢተኞች፡ እብሪተኞች፡ የአምልኮ መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል” እንደሚል እኔ እሰባለሁ።

72 በጣም ደኅንነታችን የተጠበቀ መስሎን፡ በምንኖርበት በዚህ ዘመን፡ እነሆ፡ ሩሲያ፡ በድንገት በሳይንስ ከአምስት ዓመት ቀድማን ትገኛለች፡ ብዬ እሰባለሁ።

73 ወደ ብዙ ግብዣዎች ሄደናል፡ በኃጢአትም ውስጥ በጣም ተዘፍቀናል። ቤተክርስቲያኒቱ በጣም ተኝታለች፡ ከእንግዲህ ስለ ጸሎት ስብሰባዎች ግድ የላትም፡ ግድየለሾችም ሆነዋል። እነርሱም፡ ጭምር፡ በእውነተኛውና፡ በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ ላይ ድምፃቸውን ያነሳሉ፡ እርሱንም ሊቀበሉት አይፈልጉም።

በጣም በሃይማኖት ተቋም የተከፋፈሉና፡ በውጫዊ ድምቀት ያጌጡ ናቸው! ለጸሎት ስብሰባዎች ጊዜ የላቸውም፡ ጊዜያቸውን በቴሌቪዥንና በፊልም ማሳያ ቤቶች፡ በማንከራተት፡ በሰካር ድግሶችና በመሳሰሉት ያሳልፋሉ። ይህ እውነት ነው!

74 ይህ የድሮ ፋሽን ሊመስል ይችላል፡ ነገር ግን ዛሬ አገሪቱ የምትፈልገው ይህንን ነው። በወንጌል ላይ የጎማ ጓንት አድርጎ እንደመነካካት ያለ፡ ለዘብተኝነት በጣም በዝቷል። በባዶ እጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ መያዝ አለበት። በእውነት!

75 ቢሊ ግራሃም፡ ከሳምንት ወይም ከሁለት ሳምንት በፊት ባስተላለፈው፡ በአንዱ መልእክቱ፡ “ሩሲያ በፈለገች ጊዜ፡ ይህች አገር የሩሲያ ሳታላይት ጥገኛ ልትሆን ትችላለች፡” ብሎ ነበር። ታዲያ የት ነው ያለነው?

76 ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ የኤልቪስ ፕሬስሊን ሪከርዶች ገዝታችሁ፡ **ዊ ላብ ሱዚ** የሚለውን ለመስማት ከቤተ ክርስቲያን ቀርታችሁ ቤት ትውላላችሁ! በሚዛን ተመዝናችሁ፡ ቀልላችሁ ተገኝታችኋል! ምን ተፈጠረ? በግድግዳው ላይ የእጅ ጽሕፈት አለ!

77 ሩሲያውያን እኛ ምንም ልንቆጣጠረው የማንችለውን ስፑትኒክ፡ ከምድር አምስት መቶ ማይል ርቆ እንዲመጥቅ አስችላለች፥ በቀጣዮቹ ሰላሳ ደቂቃዎች ውስጥ ግማሽ ደርዘን የሚሆኑትን በአሜሪካ ላይ ሊያስማሩና፡ ደውለው “እጅ ስጡ፡ ካልሆነ ግን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አመድ ትሆናላችሁ፡” ሊሉ

ይችላሉ። ይህንን ማድረግ ይችላሉ። እነርሱን ለማስቆም ማድረግ የምንችለው ምንም ነገር የለም። እጃቸው ውስጥ ነው፡ ደም አልባ፡ ልበ ቢስ፡ እግዚአብሔርን በማይፈራ ኮሚኒስት እጅ ውስጥ ነው! እግዚአብሔር ኃጢአት እንዲጋለጥ የሚጠቀመው እንደዚህ ያለውን ነው። እርግጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ካነበባችሁ፡ እንደ ራእይ መጽሐፍ ትንቢት ሩሲያ ይህን ማድረግ አለባት። እኔ... እናንተ የትንቢት መምህራን ከዚህ ልትለዩ ትችላላችሁ፡ ነገር ግን ነገሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ብቻ ጠብቁ። ሩሲያ እዚህ የተቀመጠችው ለዚሁ ዓላማ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይላል።

78 አሁን እነሆ ስፑትኒክ አላት። እኛም በቀደም ምሽት አንዱን ለማስወንጨፍ ሞከርን፡ እንደ እነርሱ የምናደርግ መስሎን ነበር፥ ከመሬት ሦስት ጫማ ብቻ ከፍ አለና፡ ከሸፈ። ከመጠን ያለፈ ሮክ-ኤንድ-ሮልና ኃጢአት! በሚዛን ተመዝነን፡ ቀልለን ተገኝተናል። አምላክ ሆይ፡ ማረን!

79 ምን ልናደርግ ነው? እነዚያን ስፑትኒኮች በሚሳይል አስገጥመው ቢልኩና፡ “እጅ ስጡ፡ ካልሆነ ግን በአምስት ደቂቃ ውስጥ የዐመድ ክምር ትሆናላችሁ” ቢሉ፡ ምን ይፈጠራል? እርግጥ ነው፡ መንግሥታችን፡ የሰውን ሕይወት ለማዳን ሲል፡ እጅ ይሰጣል። ሊያደርጉ የሚችሉት ብቸኛው ነገር ይህ ነው።

80 ያኔ ለአንዳንዶቻችሁ አሜሪካውያን፡ እዚህ ላለነው ለሁላችንም፡ እዚህ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ፡ ማለቴ በሃገር ደረጃ፡ በአገር ደረጃ ምን ይፈጠር ይሆን!

81 እናንተ ከንፈሮቻችሁን እንደ ጽጌረዳ አበባ አድርጋችሁ በመቀባት በየመንገዱ የምትሮጡ፡ በማዕዘን ላይ ሆኖ ወንጌልን በሚሰብክ ሰባኪ ላይ፡ የምትስቁ ብልጣብልጥ ሴቶች። እናንተም ከማስተዋላችሁ ይልቅ ግትርነታችሁ የሚበልጥባችሁ ወጣቶች!

82 ማታ ቤት ውስጥ ከእማማ ጋር ተቀምጠህ ቴሌቪዥን የምታየውና በወንጌል ላይ የምታላግጠው፡ አባት፡ ምን ልውጥህ ነው፡ ልጃችሁ ጁኒዮር በፈጣን መኪናው ሲዞር፡ እህቱ ደግሞ የሆነ መዝናኛ ውስጥ፡ ሮክ-ኤንድ-ሮል ስትጨፍር በእናንተስ ላይ ምን የሚደርስባችሁ ይመስላል? እናንተ ግን ቴሌቪዥን እያያችሁ፡ በወንጌል ላይ ትቀልዳላችሁ!

83 የቤተ ክርስቲያን አባል ሆይ፡ አንተስ ምን ይውጥሃል? ፍጻሜህስ ምን ይሆን? በከተማዋ ባሉ ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት መዝገቦች ላይ ሁሉ፡ ስምህ ሊኖር ይችላል፡ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ደም ጥበቃ ስር ካልሆንክ፡ ከሚጠፉት ጋር ትጠፋለህ፡ ለአንተ ምንም ተስፋ የለም።

84 ምን ይፈጠር ይሆን? ያው ሳተላይቱ ስፑትኒኩ እዚያ አለ። ምን ይፈጠራል? አገሪቱ እጅ ትሰጣለች፡ እርግጥ ነው፡ መንግሥት ሊያደርገው የሚችለው ብቸኛው የሚገባ ነገር እሱ ነው።

85 ከዚያስ ምን ይሆናል? ማዕበል በማዕበል ላይ፡ መርከብ ሙሉ ወታደሮች፡ ማዕበል በማዕበል ላይ፡ በአውሮፕላኖች፡ በዚህች አገር ላይ ያርፉ ነበር። ሴቶች በየመንገዱ ይደፈራሉ። ምን ልታደርጉ ትችላላችሁ? አገሪቱ የእነርሱ ትሆናለች። ከቤታችሁ ትባረራላችሁ፡ እነርሱም ይወርሱታል።

86 በዚያን ጊዜ እናንተ ወጣት ልጃገረዶችና፡ ወጣት ወንዶች፡ ሁላችሁም ምን ትሆኑ ይሆን? ኃጢአት ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል፡ የትኛውም አገር ቢሆን፡ ወይም የሚያደርገው ማንኛውም ሰው ቢሆን፡ በግለሰብም ሆነ በአገር ደረጃ፡ ዋጋ መከፈሉ አይቀርም። ጨካኝ፡ አምላክ የለሽ፡ ጺማም-አገጫም፡ የኮሚኒስት ወታደሮች ሚስቶቻችሁንና፡ ወጣት ልጃገረዶቻችሁን ይዘው ይደፍሯቸዋል፡ እናንተም ቆማችሁ ከማየት በቀር፡ ምንም ልታደርጉት የምትችሉት ነገር አይኖርም።

87 ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? ምክንያቱም እነዚህን የሮክ-ኤንድ-ሮልና የኃጢአት የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን፡ እንዲሁም ከተፈጥሮ በላይ የሆነውን መተርጎም የማይችል ቀዝቃዛና መደበኛ ሰባኪን ስለሰማችሁ ነው። ጽሕፈቱ በግድግዳው ላይ ተጽፏል! ተጽፏል! በሚዛንም ተመዝነን፡ ቀልለን ተገኝተናል።

88 ይህ መቼ ሊሆን ይችላል? ነገ ጎህ ሳይቀድ ሊሆን ይችላል። ማን ሊያስቆመው ይችላል? እስቲ ሞክሩት። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚሆን ይናገራል።

89 ነገር ግን ልንገራችሁ፡ ይህ የሕያው እግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ አይነካም፡ በዚያን ጊዜ ሄደናልና!

90 ስለዚህ፡ ወዳጄ ሆይ፡ ስማ። ነገሩ እንዲህ የቀረበ ከሆነና፡ ጽሕፈቱንም በግድግዳው ላይ ካየን፡ ይህ ነገር እንዳይሆን አሁን ሊያግደው የሚችል ምንም ነገር የለም።

91 አሜሪካ ተሰብኮላታል፡ መለኮታዊ ነገሮችም ተከናውነዋል፡ እነርሱ ግን ያለማቋረጥ በላዩ ላይ እየረገጡ ያልፋሉ።

92 የሆነ አገር ሄዳችሁ መነቃቃት ብታደርጉና፡ በአንድ ሳምንት ውስጥ አርባ ሰዎች ቢለወጡ፥ ከስድስት ሳምንት በኋላ ብትመለሱ ግን፡ አራት እንኳ አታገኙም። አሮጌው ኩሬ በመረብ ተጎትቶ ደርቋል። እግዚአብሔር የመረጣቸው የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ናቸው። የመጨረሻው ሰው ሲገባ፡ ያ በሩን ይዘጋዋል ሁሉም ያበቃል።

93 ምሕረት ከተናቀ በኋላ ከፍርድ በቀር የሚቀር ምንም ነገር የለም። ይኸው የመንገዱ መጨረሻ ላይ ደርሰናል።

መለኮታዊ ነገሮች እየተከናወኑ ነው፡ ነገር ግን ተሳልቀውባቸዋል አላገጠውባቸዋልም። በመጨረሻም፡ እግዚአብሔር በገዛ ኃይሉ፡ በተወደደው ልጁ፡ በቤተ ክርስቲያኑ በኩል ሊሠራ መጥቷል፡ እነርሱ ግን ይህ መናፍስት ጠሪነት፡ ወይም፡ ከዲያብሎስ ነው ይላሉ። ከፍርድ በቀር ሌላ ምን ሊቀር ይችላል? ይኸውላችሁ በግድግዳው ላይ ያለው ጽሕፈት!

94 ነገር ግን፡ ያ እንዲህ የቀረበ ከሆነ፡ ማንኛውም መምህር መከራው ከመጀመሩ በፊት ቤተ ክርስቲያን በንጥቀት እንደምትሄድ ያውቃል። ስለዚህ ያ እንዲህ የቀረበ ከሆነና፡ ነገ ጠዋት እንኳ ሊሆን የሚችል ከሆነ፡ ንጥቀቱስ? ከዚያም ይልቅ የቀረበ ነው! ኦህ፡ የጌታ ስም የተባረከ ይሁን! የጌታ መምጣት ቀርቧል። ጽሕፈቱ ተጽፏል፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ተጽፏል፡ እኛም ይህን ለማየት በሕይወት አለን።

95 በድምፄ ግፊት፡ በዚህች ሰዓት ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ትቀበላላችሁን? "ንስሐ ግቡ፡ ተጠመቁ፡" ጴጥሮስም፡ "ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡

እያንዳንዳችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፥ የተሰፋው ቃል ለእናንተና፡ ለልጆቻችሁ፡ በሩቁም ላሉት ሁሉ ነውና። እንድንበት ዘንድ፡ ከሰማይ በታች ለሰዎች የተሰጠ ሌላ ስም የለምና" አለ። የክርስቶስ ካልሆናችሁ በቀር! ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ጴንጤቆስጤ፡ ናዝራዊ፡ ካቶሊክ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ ነገር ግን የክርስቶስ እስክትሆኑና፡ ክርስቶስ ወደ እናንተ እስኪመጣ ድረስ የጠፋችሁ ናችሁ፡ ይህም በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን አዲስ ልደት ነው። ዛሬ ምሽት ስንጸልይ፡ እርሱን ተቀበሉ።

96 ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ሳለ፡ ይህንን እጠይቃችኋለሁ፡ ይህ ታላቅ ነገር እንደሚሆን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ዛሬ ምሽት ከባለቤትህ ጋር ልትተኛ ትችላለህ፡ ጠዋት ግን እሷ ልትወሰድ ትችላለህ። እናንተ፡ አባትና እናት፡ ዛሬ ምሽት፡ ትንንሽ ልጆቻችሁን ስማችሁ ልታስተኙዋቸው ትችላላችሁ፡ ነገ ጠዋት ግን አልጋው ባዶ ሊሆን ይችላል። ወይዘሮ ጆንስ ምን እንደሆነች ለማወቅ፡ ወደ መንገድ ትሮጣላችሁ፡ እሷም። ተወስዳለች። ንጥቀቱ ቀርቧል፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን በግልጽ አስቀምጦታል።

97 በዚህ ስብሰባ ላይ፡ እንደ አ—አስተዋይ ወ—ወንዶችና፡ አስተዋይ ሴቶች ዕድሉ እያላችሁ፡ ለምን ያንን የልባችሁን ጥሪ ሰምታችሁ፡ "ጌታ አምላክ ሆይ፡ በዚያ የዘላለም ሕይወት ሙላኝ፡" አትሉም። ምክንያቱም፡ መንፈሳችሁ አሁንም የአእምሮ ግንዛቤ ብቻ ከሆነ፡ ከምድር ጋር የተጣበቃችሁ ናችሁ። ነገር ግን ከሰማይ የወጣው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ፡ ወደ ልባችሁ ሲመጣና በውስጣችሁ መንፈስ ቅዱስን ሲሰጣችሁ፡ መከራው በሚመጣበት ጊዜ፡ ያ መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ወደ ፈጣሪው ይመለሳል፡ እናንተም ከእርሱ ጋር ትሄዳላችሁ። ምንም ያህል ሃይማኖተኛ ብትሆኑ፡ የሚወስዳችሁ የሆነ ነገር መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ከሌለ በቀር አትሄዱም።

98 ዛሬ ምሽት፡ ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ ይህን መልእክት ሰምታችሁ፡ ወደ ክርስቶስ እጆቻችሁን በማንሳት፡ "አምላክ ሆይ፡ በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ። ብትመጣም፡ ከአንተ ጋር መሄድ እፈልጋለሁ፡" የምትሉ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን ታነሳላችሁ? እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሁሉም ቦታ እንስተዋል። በትክክል፡ ሁለት መቶ፡ ወይም ከዚያ በላይ፡ እጆች በአየር ላይ ተነስተዋል።

99 ኃጢአተኛ ወዳጄ ሆይ፡ ክርስቶስን ፈጽሞ ተቀብለህ የማታውቅ ከሆነ፡ በዚህ ሰዓት እጅህን እንስተህ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ማረኝ፡" ትላለህ? እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። እግዚአብሔር ይባርካችሁ እዚህ፡ እናንተንም እዚያ ኋላ ያላችሁ። ሌላ ሰው፡ "ጌታ ሆይ፡ አሰበኝ ብቻ" የሚል። እግዚአብሔር ይባርካችሁ እዚህ፡ እዚህም ታች። ጌታ ከእናንተ ጋር ይሁን። "ጌታ ሆይ፡ አሰበኝ። ዓይኖቼ አሁን ተከፍተዋል። ለረጅም ጊዜ ክርስቲያን ነኝ ብዬ ብመሰክርም፡ ዳግመኛ መወለድ ምን እንደሆነ ግን ፈጽሞ አላውቅም ነበር። መንፈስ ቅዱስን ፈጽሞ አልተቀበልኩም።"

100 "ስለዚህ፡ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ ወደ መንግሥቱ ከቶ ሊገባ፡ ወይም መንግሥቱን ሊያይ እንኳ አይችልም።"

101 እጆቻችሁን እንስታችሁ፡ እንዲህ፡ "ኦ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፡ ማረኝ። ለቤተ ክርስቲያን ስትመጣ፡ እኔንም ውሰደኝ" ትላላችሁን? እግዚአብሔር ይባርክሽ፡

እመቤት። ሌላስ? “አምላክ ሆይ፡ አሰበኝ።” ጌታ ይባርክህ፡ ወዳጄ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። “አምላክ ሆይ፡ አሰበኝ”። እግዚአብሔር ይባርክህ እዚህ ያለኸው፡ ወጣት። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እዚያ ያለሽው እመቤት። እዚያ ኋላ ያለሽው፡ ወጣት፡ እዚያ ኋላ። አንቺም እዚያ ኋላ ያለሽው፡ እመቤት። “እግዚአብሔር ሆይ፡ ጽሕፈቱ በግድግዳው ላይ ሲሰፍር ባየሁ ጊዜ፡ ማረኝ። በቂ ማስተዋል አለኝ፡” እንዲህ በሉ፡ “ዛሬ ምሽት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው ነገር፡ የታሪክ ድግግሞሽ መሆኑን ለማወቅ፡ በቂ ማስተዋል አለኝ” በሉ።

102 መጨረሻው ላይ ነን። ምንም ሊረዳ የሚችል ነገር የለም። ዓለምን የሚያጠፋው ነገር ኃጢአተኛ በሆኑ ሰዎች እጅ ነው።

103 ጥቂቶች ብቻ ቀርተዋል። ወደ ክርስቶስ እንዲመጣ ቀድሞ ከተወሰነው መካከል አንተ የመጨረሻው ልትሆን ትችላለህ። ያ የመጨረሻው ሲመጣ፡ ፍርድ ይመታል፥ አንድ ነገር ገና ይጎድላል፡ ያም አንተ ልትሆን ትችላለህ። በምንጠብቅበት በዚህ ሰዓት ዛሬ ምሽት እርሱን ትቀበላለህን?

104 ወደ ሃያ፡ ሰላሳ የሚጠጉ እጆች ተነስተዋል። አሁን እዚህ ሰዎችን ወደ ፊት ቦታ ስለሌለን፡ የመሠዊያ ጥሪ የምናደርግበት፡ በቂ ቦታ የለንም። ነገር ግን በእርግጠኝነት፡ እጠይቃችኋለሁ፡ ኦህ፡ ቅን ሁኑና የማስጠንቀቂያውን ድምፅ ስሙ። ቅን ሁኑና ባላችሁበት ሆናችሁ፡ ክርስቶስን እንዲህ ብላችሁ ጠይቁት፡ “ጌታ ሆይ፡ እኔን ኃጢአተኛውን፡ ማረኝ፡ ከምሕረት መጋረጃ ባሻገር ሳልሄድ ተቀበለኝ። የጸጋዬ ቀን ሳያልፍ፡ ጌታ ሆይ፡ ማረኝ” በሉ። እርሱም ያደርገዋል።

እኔም ከእናንተ ጋር ስጸልይ እናንተም እንደዚያ ጸልዩ።

105 የተባረክህ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ምሽት በአስፈሪ ሁኔታ ውስጥ ቆመናል። ቃልህን ስናነብ፡ በማንኛውም ሰዓት ሬዲዮኖች ድንገተኛ ዜና ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ፡ የሮክ-ኤንድ-ሮል ሙዚቀኞች **አምላኬ ሆይ፡ ወደ አንተ፡ እቀርባለሁ** ብለው ሊዘምሩ እንደሚችሉ እናውቃለን፡ ያኔ ግን በጣም ዘግይቷል፡ ፍርድ መጥቷልና። ሚሳይሎች ወደ እኛ ተደቅነውብናል። ማይል በማይል ላይ፡ ቶን በቶን በማከታተል፡ ም—ምድርን-ጠራርጎ የሚያጠፋ አቶሚክ ኃይልና፡ የመሳሰሉት፡ ዓለምን በእሳት ሊያጋዩ ይችላሉ። ይህም ኃጢአተኛ በሆኑ ሰዎች እጅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ እንደሚሆን ተናግሯል። እኛም በግድግዳው ላይ ያለውን ጽሕፈት እያየን ነው።

106 ጌታ አምላክ ሆይ፡ እንዲህ ዓይነቱን መልእክት ለሕዝብ ለማድረስ እኔ ብቁ አይደለሁም። እንዲህ ያለውን ርዕስ ለመናገር፡ እዚህ ሰቆም፡ ምን ያህል ትንሽ እንደሆንኩ ይሰማኛል፡ ነገር ግን ይህን ለማድረግ ባለመቻሌ በኔ በኩል ያለውን ድክመት ይቅር ትለኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። ነገር ግን በሆነ መንገድ፡ መልእክቱ አንተ በምትፈልገው መንገድ፡ በልባቸው ውስጥ እንዲሰርጽ፡ ከልቤ፡ እለምንሃለሁ፡ ምክንያቱም ሰዓቱ እየቀረበ መሆኑን አያለሁና። አምላክ ሆይ፡ ማረን፡ እያንዳንዱንም አድን፡ በመንፈስ ቅዱስም ሙላቸው። በመለኮታዊ ቸርነትህ ተጠቅልለው፡ ያንተ ልጆች ይሁኑ፡ ከጌታ ኢየሱስም ደኅንነትን ይቀበሉ።

107 ምክንያቱም አገራችን ደኅንነቷ የተጠበቀ አይደለም፡ እኛ ግን የተጠበቀ መስሎን ነበር፡ የባቢሎን መንግሥትም እንዲሁ አስቦ ነበር፡ ነገር ግን በዚያ

ሁሉ ጊዜ አንዲት ክፉ ሕዝብ መንግሥት እየሠራች ነበር። አሁን ከእኛ መቅደማቸውን እስከምናውቅ ድረስ፡ አንዲት ክፉ ሕዝብ እየሠራች ነበር፡ እኛም በእነርሱ ምሕረት ሥር ነን።

108 ጌታ ሆይ፡ ቤተ ክርስቲያን በአንተ ምሕረት ሥር ናት። እነርሱ ያጠፋሉ፡ አንተ ግን ቤተ ክርስቲያንህን ትወስዳለህ። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ምሽት፡ በእንክብካቤህ ሥር አድርገን። ስለ ኢየሱስ ስትል ባርከን፥ በሰሙም እንጸልያለን። አሜን።

109 ለጥቂት ደቂቃ፡ በዝግታ። በአክብሮት ሁኑ።

> በዝግታና በለስለስ ድምፅ ኢየሱስ እየጠራ ነው፡
> አንተን እየጠራ ነው...

አሁን እየዘመርን ሳለ፡ ራሳችሁን መርምሩ።

> ... በደጃፉ ላይ ሆኖ እየጠበቀና እየተመለከተ ነው፡
> እኔንና አንተን እየጠበቀ ነው።
>
> ወደ ቤት ና... (የት? ወደ ላይ፡ ወደ ላይ ከፍ በል።)
> እናንተ የደከማችሁ፡ ወደ ቤት ኑ፡
> በቅንነትና፡ በለሰላሳ ድምፅ፡ ኢየሱስ እየጠራ ነው፡
> ኃጢአተኛ ሆይ፡ ወደ ቤት ና፡ ይላል!

[ወንድም ብራንሃም **በዝግታና በርህራሄ** እያለ አዜመ—አርታዒ።]

110 ኦህ፡ አሁኑኑ ቢሆን ምንኛ ድንቅ ጊዜ ይሆን ነበር! ኦህ፡ ምንም አይደለም፡ እርሱ በፈለገው በማንኛውም ሰዓት ይሁን። አሜን! እርሱን በማወቄ በጣም ደስተኛ ነኝ። እዚህ እየመነመነ ያለው፡ ይህ አሮጌና ደካማ አካል፡ በአንድ አፍታ፡ በዐይን ጥቅሻ ውስጥ እንደሚለወጥ በማወቄ በጣም ደስተኛ ነኝ። ለዘላለም ለመኖር እንደገና ወደ ወጣትነት እመለሳለሁ።

> አዛውንቱ በዚያ ለዘላለም ወጣት ይሆናል፡
> በቅጽበት ጊዜ ውስጥ ተለውጦ፥
> የማይሞት ሆኖ፡ በአምሳሉ ይቆማል፡
> ከከዋክብትና ከፀሐይ ይልቅ ይበራል።

ምን ዓይነት ዕድል ነው! ቸል አትበሉት።

> ኦህ፡ በዚያ የዘላለም ቀን፡ "መልካም አደረግህ፡"
> እንዲልህ ምንኛ ትመኝ ይሆን!
> ያንን የተወደደ አዳኝ ከልብህ አትመልሰው፡
> አትመልሰው። (ይህች ምሽት ምሽትህ ትሁን።)

111 በፍጹም ልባችሁ እርሱን የምትወዱና፡ እርሱ ቢመጣ ዝግጁ የሆናችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? ኦህ፡ ምንኛ አመስጋኞች ነን! አሁን በውስጣችሁ፡ የታጠባችሁ ሆኖ አይሰማችሁም? ወንጌል፡ በቃሉ ውሃ ታጥበናል። አጠገባችሁ ያለውን ደርሳችሁ፡ የሆነ ሰው እጅ ጨብጡና፡ እንዲህም በሉ፡ "እግዚአብሔር ይባርክህ። በጣም ደስ ብሎኛል። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ፒልግራም። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ፡ ወንድሜ።" በመንገድ ላይ የምንጓዝ መንገደኛ ሰዎች ነን።

> በመንገድ ላይ ያለን መንገደኞች ነን፡

በዚያ ታላቅና ጥንታዊ ጎዳና ላይ እየተጓዝን፡
ጌታ ሆይ፡ የጥንቱ-ክርስቲያን መሆንን እመርጣለሁ።
ከሌላው ሁሉ እኔ ከማውቀው።

112 አሁን በዚህ የትሕትና ጊዜ ውስጥ እንዳለን፡ የጸሎት ሰልፍ ለመጥራት ሰዓቱ ትንሽ የረፈደ ይመስለኛል። እ... ይህ ያህል ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ ክርስቶስ በመምጣቱ፡ መንፈስ ቅዱስ በጣም ደስ እንደተሰኘ አምናለሁ። አሁን በፍጥነት ቤተ ክርስቲያን ፈልጉ፡ ጥሩና በመንፈስ-የተሞላች ቤተ ክርስቲያን ፈልጋችሁ፡ ተጠመቁ ቤተ ክርስቲያን ሁኑ፡ በሕይወት እስካላችሁ ድረስም በዚያው ቆዩ።

113 ክርስቶስ አደርጋቸዋለሁ ብሎ ቃል የገባቸው ሥራዎች ምንድን ናቸው? እርሱም፡ “እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ” አለ። ስለዚህ፡ ህልውናው እዚህ አለ። ስለዚህ፡ አውቃለሁ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ኢየሱስ እዚህ እንዳለ፡ ያለ አንዳች ጥርጥር፡ እ—አውቃለሁ። እዚህ አንድ ሰው አለ፡ በገሊላ የተመላለሰው ያው ሰው እርሱ ነው። በደሙ የዋጃችሁ፡ በቁስሉ የፈወሳችሁ ያው ሰው እርሱ ነው። እርሱም ያው የሆነው ጌታ ኢየሱስ ስለሆነ፡ ያኔ ያደረጋቸውን ሁሉ ለማድረግና ለመፈጸም እዚህ አለ።

114 አሁን ለአንድ አፍታ፡ በዝምታ እንጸልይ። እኔ የመንፈስ ቅዱስን አሳብ ለማግኘት ስሞክር እናንተ በጸሎት ቆዩ።

115 ስለዚህ፡ ያ አስደናቂ ሙዚቃ፡ ዛሬ ምሽት በሥቃይ ውስጥ ያሉ ሰዎች ያንን ለመስማት ምንኛ በወደዱ ነበር! ዛሬ ምሽት እናንተ በተቀመጣችሁበት ወንበር ላይ ምናልባት ተቀምጠው የነበሩ፡ ወንጌልንም የሰሙና፡ አልፈው የሄዱ ሰዎች፡ ዛሬ በሥቃይ ውስጥ ናቸው፡ እናንተ የተቀመጣችሁበትን ወንበር ለመያዝ ምንኛ በወደዱ ነበር፡ አሁን ግን በጣም አልፎባቸዋል።

116 ጌታ ሆይ፡ ሰማያትንና ምድርን የፈጠርህ፡ የተባረከውን ጌታ ኢየሱስን ወደዚች ምድር የላክህ፥ በእርሱም የመንፈስ ሙላት ይኖራልና። አንተም እንዳልከው፡ በአንደበቱ፡ “እኔ የወይን ግንድ ነኝ፡ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። የወይን ግንድ በራሱ ፍሬ አይፈራም፣ ነገር ግን ቅርንጫፎቹ ፍሬ ያፈራሉ” ብለሃል። አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ምሽት በመካከላችን ራስህን እንድትገልጥ፡ እጸልያለሁ፡ ይህም ሕዝቡ፡ አሁን የተሰበከው መልእክት፡ ከአንተ የመጣ መሆኑን፡ እንድንዘጋጅም እየጠነቀቅከን እንደሆነና፡ የመጨረሻዎቹ ቀናት መቅረባቸውን ያውቁ ዘንድ ነው።

117 ጌታ ሆይ፡ እዚህ ተቀምጠው ያሉ የታመሙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይፈወሱ ዘንድ ብርታት ስጣቸው፡ ይህን የምንጠይቀው፡ ለእግዚአብሔር ክብር ነውና። አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ እንደ ሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ራሳችንን ለአንተ ስንሰጥ፡ እዚህ ያለው፡ እያንዳንዱ፡ እጅ እንዳነሳ እገምታለሁ። እናም ዛሬ ማታ፡ ጌታ ሆይ፥ ለእኛ ልዩ የሆነ ነገር እንድታደርግ፡ እጠይቅሃለሁ። አሁንም ይሁንልን እነዚህ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ፡ በዚያ አይነት እምነት፡ በዚያ አይነት እምነት፡ ራሳቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ፥ እና እኔም ራሴን ለአንተ አሳልፌ እንድሰጥ አንተም በስጦታዎችህ አማካይነት እንድትሰራና፡ በመካከላችን ራስህን እንድታጸና፥ በመካከላችን እንግዶች ሊኖሩ ይችላሉና። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

118 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... ከፍርድ በፊት ሁልጊዜ ምሕረትን ያሳያል። አገልጋዮቹ እዚያው ሆነው እንዲጸልዩ፡ እጠይቃለሁ። እንጸልይ።

119 አሁን ደግሞ፡ በተለይ፡ እኔ እየሰበክሁ ነበርኩ፡ ም—ምናልባት እዚህ ፊት ለፊት ያላችሁ ወይም፡ የትም ያላችሁ ሰዎች፡ ይህንን ማለት እንድትጀምሩ እጠይቃለሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "በድካማችን ሊራራልን የሚችል ሊቀ ካህናት ነው" ይላል። እንግዲያውስ፡ እርሱ፡ ትናንት የነበረው ያው ሊቀ ካህናት ከሆነ፡ ዛሬም እርሱ ያው ከሆነ፡ ስለዚህ የትናንትና ተመሳሳይ ስራ፡ ማለትም እርሱ ያው ከሆነ ዛሬም ይሠራዋል። ልክ ነው? ስለዚህ አሁን ሊነካ የሚችል ከሆነ፡ እናንተም በድካማችሁ ስሜት ንኩት፡ እርሱም ይመልስላችሁ።

120 እስቲ አስቡት፡ በአንድ ወቅት፡ እንደዚህ ባለ ሕዝብ መካከል ቆሞ ሳለ፡ ጴጥሮስ የተባለ፡ ወይም ስሙ ስምዖን የሆነ አንድ ሰው መጣ። እርሱም፡ "ስምህ ስምዖን ነው። የዮና ልጅ ነህ። ነገር ግን ከእንግዲህ ጴጥሮስ ትባላለህ" አለው። ማን ሆነ? ተወዳጁ ሐዋርያ።

121 ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶት፡ ወደ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "ተንኮል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ እነሆ።" በሌላ አነጋገር፡ "ክርስቲያን፡ ቅን ሰው" ማለቱ ነው።

እርሱም፡ "ረቢ፡ ከየት ታውቀኛለህ? "

122 ኢየሱስም፡ "ፊልጶስ ሳይጠራህ፡ ከበለስ ዛፍ በታች ሳለህ አይቼሃለሁ፡" አለው።

123 የደም መፍሰስ ችግር የነበረባት ያቺ ሴት መጣች። እርሱም ጉባኤውን ተመለከተ።

124 እነርሱ ሥራው ከዲያብሎስ ነው ብለው አሰቡ፡ በልባቸውም "እርሱ ብዔልዜቡል ነው፡" አሉ። እርሱም አሳባቸውን ተረዳ። ልክ ነው አይደል?

125 እንዲህም አለ፡ "አብ አስቀድሞ ሳያሳየኝ ምንም አላደርግም። እኔ የማደርገውን ሥራም፡ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" ስለዚህ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚሰራ ከሆነ፡ እርሱ መሆን አለበት፡ ምክንያቱም ቃሉ ነውና።

126 አሁን ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ከዚህ ጉባኤ መካከል፡ ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች፡ ልብሱን ለመንካት የሚበቃ እምነት እንዲኖራቸው ጌታ ቢፈቅድ፡ እርሱም በመንፈሱ መጥቶ ልክ እዚህ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያደርግ እንደነበረው በትክክል ቢሠራ፡ ሁላችሁም እርሱን እንደ ፈዋሻችሁ ለመቀበል ትስማማላችሁ? ይህን ታደርጋላችሁ? የምታደርጉ ከሆነ፡ "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] ይህንን እንዲሰጠን፡ ጸሎቴ ነው። አሁን እናንተ ብቻ ጸልዩ። እናንተ...

127 ከእናንተ መካከል መፈወስ የሚፈልጉ የታመሙ ሰዎች ስንት ናችሁ? እጃችሁን አንሱ። እሺ፡ መፈወስ የሚፈልጉ የታመሙ ሰዎች፡ በሁሉም ቦታ።

128 አሁንም፡ በዚህ ሕንፃ ውስጥ ማንም ሰው ካለ... እኔ እያየሁት ያለሁትን እንዳቸውም አላውቃቸውም።

129 እዚህ የተቀመጠችው ሮዜላ ትመስለኛለች፡ ያቺ የአልኮል ሱሰኛ የነበረችውና፡ አልኮል ሱሰኛ የነበረች፡ ሐኪሞችም ተስፋ የቆረጡባት፡ አልኮል ሱሰኛ የነበረችው ትንሽ ልጅ። እርሷ፡ የሆነ ቦታ በስብሰባ ውስጥ የተጠራችው፡

በጌታ በተጠራች ጊዜ አይቻት እንደማላውቅ ወይም እንደማላውቃት እራሷ ታውቃለች። ጌታም ስለ ሕይወቷና ስለ ሁኔታዋ ሁሉ ነገራት፡ ደህና እንደምትሆንም ነገራት። ዛሬ ምሽትም እነሆ እዚህ አለች፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ማሳያ ምስክር ናት። ሐኪም ከሐኪም በኋላ እስኪተዋት ድረስ፡ ሰካራም የነበረች፡ አልኮሆሊክስ አኖኒመስ ሳይቀሩ። አውቃታለሁ።

130 ነገር ግን፡ ከእሷ ውጭ፡ እዚህ ግራጫ ልብስ ለብሶ፡ ወደ እኔ የሚመለከተው ወንድም፡ አበባ የሚያመጣልን ወንድም እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። ልክ ይመስለኛል። ሰሙ አሁን—አልመጣልኝ አለ። በቅርቡ፡ ከወንድም ቦዝ፡ ከሹልስ፡ ከወንድም ሹልስ ጋር እቤቴ መጥቶ ነበር።

131 ከዚህ ውጭ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ወንድም ፍሬድ ሶሰማንን በሆነ ቦታ ያየሁት መሰሎኝ ነበር፡ አሁን ግን የት እንደነበር ረሳሁት። ሆኖም፡ እርሱ፡ እዚህ የሆነ ቦታ ነበር።

132 ሌ—ሌላ ማንንም አላውቅም። እግዚአብሔር ግን ሁላችሁንም ያውቃችኋል። ብትጸልዩና እግዚአብሔርን ብትጠይቁት፡ እምነታችሁን ፈትኑት።

133 አሁን ማንም ወዲያና ወዲህ አይበል፡ ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች በጣም በአክብሮት ሁኑ። (አሁን ፈቀዳችሁ ከሆነ **እመን ብቻ** የሚለውን እንዘምር።) እናም ለጥቂት ጊዜያት በተቻላችሁ መጠን በአክብሮት፡ ዝም ብላችሁ ተቀመጡ።

134 እስቲ አስቡት፡ ክርስቶስ ቃል ገብቶአል። "ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ዓለም አያየኝም፥ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ እኔ…" ("እኔ፡" እንጂ ሌላ አይደለም። "እኔ" የግል ተውላጠ ስም ነው።) "… እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ። እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እናንተ ደግሞ፡ ታደርጋላችሁ።" "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ፡ ለዘላለምም ያው ነው።" ይህ እውነት ነው? እውነት መሆን አለበት።

135 እንግዲህ፡ ጌታን በጣም አመሰግናለሁ። እኔም… ከፈለጋችሁ ራሳችሁን ቀና ማድረግ ትችላላችሁ።

136 እዚህ ጥግ ላይ፡ አንዲት እመቤት ተቀምጣለች። ጥቁር ሴት ናት። እመቤት፡ እኔ አላውቅሽም። እግዚአብሔር ግን ያውቅሻል። ነገር ግን ያ ብርሃን አሁን በሴቲቱ ላይ ቆሟል። እሷ… ጌታ ችግርሽ ምን እንደሆነና፡ ስለ ምን እየጸለይሽ እንደሆነ ቢገልጥልኝ፡ ሊረዳሽ የመጣው ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ ታምኚያለሽ? በችግር ውስጥ ሳትሆኚ አትቀሪም፡ ወይም የምትፈልጊው ነገር አለ፡ ምክንያቱም ያውና።

137 አያችሁ፡ ወዳጆች፡ "እንግዲህ፡ እኔ አላየሁትም፡" ትሉ ይሆናል። ላታዩት ትችላላችሁ። እኔ ግን ቀጥታ እያየሁት ነው። አያችሁ? "እሺ፡ ወንድም ብራንሃም፡ አንተ በስሜትህ ልታየው ከቻልክ፡ እኔም፡ ማየት እችላለሁ፡" ትሉ ይሆናል። ኦህ፡ ኖ።

138 ጳውሎስ ያንን አይቶታል፡ ኢየሱስን በብርሃን መልክ አይቷል፡ ከእርሱ ጋር የነበሩት ግን አላዩትም። አያችሁ? ሰብአ ሰገል ኮከቡን፡ የመራቸውን ያንን ብርሃን አዩ፡ ሌላ ማንም ግን አላየውም ነበር። ያ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚሆን ነው። ስጦታዎች እንዲህ ናቸው።

139 ሴቲቱ የሳይነስ ችግር አለባት። ያ ልክ ነው። ደግሞም የልብ ሕመም አለብሽ። ያ በትክክል ልክ ነው። ስሚ፡ ስምሽ፡ “ኤሲ” ይሉሻል። እ-ህም። የአባትሽ ስም ደግሞ አፕሻየር ነው። እ-ህም፡ እ-ህም። የምትኖሪው በሰሜን ክሊቭላንድ ጎዳና ነው። አድራሻሽ 1264 ነው። ያ በትክክል ልክ ነው። አንቺ... የሆነ ነገር ነክተሻል፡ እመቤት። እኔን እንዳልነካሽኝ ግን ታውቂያለሽ።

140 በአጠገብሽ የተቀመጠችው ያቺ ልጅ፡ እርሷም፡ እየጸለየች ነው። እርሷ የምትጸልየው ለሌላ ሰው ነው፡ ያም ለእናቷ ነው፡ እናቷም ሳንባዋ ላይ የሆነ ችግር አለባት። አንቺም **ከዚህች** ሴት ጋር ዝምድና አለሽ። ምራቷ ነሽ። ስምሽም ማርጋሬት ይባላል። ልክ ነው። አብራችሁም ነው የምትኖሩት። ስትመጪና፡ ስትገቢ አያለሁ።

141 ቀጥለህ የተቀመጥከው፡ ጌታዬ፡ አንተስ ምን ታስባለህ? ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምናለህ? ታምናለህ? ጌታ ችግርህ ምን እንደሆነ ቢገልጥልኝ፡ ትቀበለዋለህ? የጨጓራ ህመም አለብህ። በትክክል። ይህ እውነት ከሆነ፡ በሁለት እግርህ ቁም። ትክክል። አንተ ሰባኪ ነህ።

“በእርግጥ፡” እናንተ፡ “የአገልጋይ ልብሱን ስላየ ነው” ትላላችሁ።

142 እሺ፡ ከዛ ውጭ ደግሞ፡ የሆነ ሰው ፕሬስቢቴሪያን እንድትሆን ይጠብቅሃል፡ አንተ ግን የጴንጤቆስጤ ሰባኪ ነህ። ልክ ነው። አሜን። ጨጓራህ የቆሰለው በጭንቀት ምክንያት ነው። ጠፍቷል። ወንድሜ ሆይ፡ ወደ ቤትህ ሂድና ተፈወስ። አሜን።

በእግዚአብሔር እመን። ዝም ብለህ አትጠራጠር።

143 እዚህ የተቀመጥሽው፡ አንቺስ ምን ታስቢያለሽ? አዎ። እ-ህም። ታምኚያለሽ? የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆንኩ ታምኚያለሽ? ወይስ፡ ከእግዚአብሔር የምትፈልጊው ነገር አለ? የምትፈልጊውን እግዚአብሔር ቢገልጥልኝ፡ ይህ መለኮታዊ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ሥራ እየተከናወነ እንደሆነ ታምኚያለሽ? ኢየሱስ እንደሚለው ልክ እንደዛው፡ ታምኚያለሽ? [ያቺ እህት፡ “በሙሉ ልቤ” አ፡አለች።—አርታዒ።] በሙሉ ልብሽ። እብጠት አለብሽ፡ ያም እብጠት ዳሌሽ ላይ ነው። ልክ ነው። ደግሞም የጨጓራ ህመም አለብሽ። ይህም በጭንቀት ምክንያት የመጣ ነው። ልክ ነው። እ-ህም። ስምሽ ኢቫ ሜይ ይባላል፡ የአባትሽ ስም ደግሞ ሬድማን ነው። የምትኖሪበት ጎዳና፡ በ1378 ዌስት 13ኛው ጎዳና ነው። በትክክል።

እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኔን ታውቂ ዘንድ፡ እዚያ የተቀመጠችው ልጅሽ ናት። ለእርሷ ጸሎት ትፈልጊያለሽ። ያች ትንሽ ልጅ የደም መፍሰስ አለባት፡ እርሱም የሚመጣባት ስትደነግጥ ወይም በጣም ስታለቅስ ነው። **ይህ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው።

ያ ትንሽ ልጅ ደግሞ ወንድሟ ነው። በትክክል። ለልጁም፡ ጸሎት፡ ትፈልጊያለሽ። እርሱ በሆድ ድርቀት ይቸገራል፡ እርሱም፡ በቅርቡ በጣም ከሰቷል። አይደል? **ይህ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርእንዲህ ይላል** ነው።

144 በአጠገብሽ የተቀመጠችው ነጭ ሴት፡ በሆነ ነገር የተረበሸች ትመስላለች። እህት፡ ታምኚያለሽ? እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ለዚህ ለአሕዛብ ትውልድ፡ በቅርቡ እንደሚመጣ ይገልጥ ዘንድ እንደላከው

ታምኚያለሽ? በዕጢ ህመም እየተሰቃየሽ ነው፡ ደግሞም የትልቅ አንጀት ችግር አለብሽ፡ እንዲሁም ትጨነቂያለሽ ነሽ። አንቺ የዚህች ከተማ ሰው፡ አይደለሽም። የመጣሽው ከዲትሮይት ነው። የምትኖሪበት፡ ቁጥር፡ 12134 ፋንድለር ጎዳና ነው። ልክ ነው። ዲትሮይት፡ ሚቺጋን። ጣሊያናዊት ነሽ። ስምሽ ቫዮላ ፖ-ሎ-... ፖሎምባ ይባላል። እ-ሃህ። በእግዚአብሔር እመኚ፡ የጠየቅሽውንም ተቀበዪ።

145 በዚህ በኩል ወረድ ብላችሁ ያላችሁ፡ እናንተስ ምን ታስባላችሁ? በፍጹም ልባችሁ ታምናላችሁ?

146 እዚያ የተቀመጥሽው ትንሸዬ እመቤት፡ አንቺስ ምን ትያለሽ? እዚያ ዳር ላይ ያለሽው እመቤት፡ በፍጹም ልብሽ ታምኚያለሽ? ደህና፡ ለነገሩ የትኛችሁም ብትሆኑ፡ ምንም አይደለም። ከእርሷ አጠገብ ያለሽው፡ የ... አንቺስ ምን ታስቢያለሽ? እኔን እያየሽ፡ የተቀመጥሽው ትንሸዬ እናት፡ በፍጹም ልብሽ ታምኚያለሽ? ስለ እርሱ ምን ታስቢያለሽ? ጌታ ኢየሱስ ካለብሽ የደም ሥር መገታተር እንደሚፈውስሽ ታምኚያለሽ? ታምኚያለሽ? ምናልባት ባልሽ የጀሮ ሕመም እንዳለበትና፡ እንዲጸለይለት እንደምትፈልጊ ብነግርሽ፥ ይበልጥ ታምኚ ይሆናል። ያ በትክክል ልክ ነው። እ-ሃህ። አሁን ታምኚኛለሽ? መጀመሪያ ላይ፡ ነገሩ አልገባሽም ነበር። ይህም ለነገሩ እንድትነቂ አድርጎሻል፡ ምክንያቱም ያኔ ፈውስሽን ተቀብለሻል።

147 ከእርሷ አጠገብ ያለሽው፡ እመቤት፡ እጅሽን አነሳሽ። ስለ እርሱ ምን ታስቢያለሽ? እግዚአብሔር ደህና እንደሚያደርግሽ ታምኚያለሽ? [እህትየዋ፡ “እንደሚችል አውቃለሁ” አለች።—አርታዒ።] ታምኚያለሽ? እሺ፡ እንግዲያውስ የአርትራይተስ ሕመምሽ ይለቅሻል። ማመን ትችያለሽ? ሃ?

148 እጅህን ያወዛወዝከው፡ ጌታዬ፡ አንተስ ምን ትላለህ? እግዚአብሔር ከልብ ሕመምህ እንደሚፈውስህና፡ ደህና እንደሚያደርግህ ታምናለህ? እንደሚያደርገው ታምናለህ?

149 አንተ፡ እርሱን እያየህ፡ የተቀመጥከው፡ አንተስ ደግሞ፡ ታምናለህ? እግዚአብሔር እንዲረዳህ ትፈልጋለህ... አንተም፡ የልብ ሕመም ነበረብህ፡ አይደል? አዎ። ደግሞም፡ ስኳር ነበረብህ። ልክ ነው። እግዚአብሔር ደህና እንደሚያደርግህ ታምናለህ? እንግዲያውስ ልታገኘው ትችላለህ።

አታምንም? በእግዚአብሔር እመን!

150 እዚህስ ምን አለ? በወንበሩ ዳር ላይ፡ የተቀመጥከው፡ ጌታዬ፡ ታምናለህ? ማመን ይገባሃል። አሁን ተፈውሰሃል። የእግር ሕመም ነበረብህ፡ አይደል? ጌታ ኢየሱስን ታምነዋለህን... ነገር ግን አሁን ለሌላ ሰው እየጸለይክ ነው፡ እርሱም ወንድምህ ነው፡ የሚገኘውም በዊስኮንሲን ነው። በቅርቡም ሳንባው ላይ ቀዶ ጥገና ተደርጎለታል። ግማሹም ወጥቷል። ልክ ነው። ታምናለህ? እንግዲያውስ የለመንከውን መቀበል ትችላለህ።

ኦህ፡ የጌታ ስም የተባረከ ይሁን!

አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በጉን አወድሰዋለሁ፡
ሕዝቦች ሁሉ ለእርሱ ክብር ስጡ፡
ደሙ እያንዳንዱን እድፍ አጥቧልና።

151 የተባረክህ ጌታ ሆይ፡ አንድ ቀን በዚያ በሰማያት ስትመጣ እናይሃለን። አሁን በመንፈሳዊ አካል እዚህ እንዳለህ እናውቃለን፡ ራስህንም ለእኛ ፍጹም በሆነ መንገድ ገልጠሃል። ጌታ ሆይ፡ ዓለም ይህንን ሊገነዘበው አይችልም። አንተ ራስህ፡ "ከእንግዲህ ዓለም አያየኝም፡" ብለሃልና እንዲህ እንዲያደርጉ አንጠብቅም። ነገር ግን ሊያዩህ የሚችሉ ልጆች እንዳሉህ እናውቃለን። የሚያውቁህ ልጆች አሉን፡ ለዚህም እናመሰግንሃለን።

152 አሁንም በታላቁ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሕንፃ ላይ እንድትመላለስና፡ እዚህ ያሉትን የታመሙትን ሁሉ፡ እንድትፈውስ እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ አሁኑኑ ለራስህ ክብርን አግኝ። ሕዝቡ በድንዛዜ ተቀምጠው አይቆዩ፡ ነገር ግን ተነስተው ይብሩ፡ ለ—ለእግዚአብሔርም ምስጋናንና ክብርን ይሰጡ። በኢየሱስ ስም።

153 በእርሱ ካመናችሁ፡ በሁለት እግራችሁ ቁሙና በፍጹም ልባችሁ አመስግኑት። በጌታ በኢየሱስም ሐሴት አድርጉ፡ አሁን ለታላቁ መለኮታዊ ክብሩ ሲል፡ እያንዳንዳችሁን ይፈውሳልና። ጌታ ይባርካችሁ። አሜን።

58-0108 የግድግዳው የእጅ ጽሑፍ
ሌን ቴክ ሀይ ስኩል
ቺካጎ, ኢሊኖይስ ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org